Client information

**Amharic**

refugee action

working with refugees to build new lives

# ያቀረቡት የጥገኝነት ጥያቄና እንዲሁም የይግባኝ ምልክታዎች በሙሉ ተቀባይነት ካጣ በኃላ ያለው የድጋፍና የመኖርያ ቤት ሁኔታ

ያቀረቡት የጥነኝነት ጥያቄ፡ በተመለከተ ከ Home Office* ገና ውሳኔ ያልተቀበሉ ከሆነ ወይም ደግሞ ገና ውሳኔ ያልተሰጠበት የይግባኝ ጥያቄ ካልዎት፡ በNASS* የሚሰጠውን ድጋፍ የመቀበል መብት አልዎት። ያቀረቡት የጥገኝነት ጥያቄ እንዲሁም የጠየቁት የይግባኝ ጥያቄ ተቀባይነት ካጣ፡ ያ የሚያገኙት የነበረ ድጋፍም ሊቀየር ይችላል።

## ያቀረብኩት የጥገኝነት ጥያቄ እና ይግባኝ ያልኩትን ጉዳይ ተቀባልነት አጥተዋል ወይ?

**በዚህ ጉዳይ እርግጠኛ ካልሆኑ ወይም ደግሞ በትውልድ አገርዎ ውስጥ የነበረው ሁኔታ ከተቀየረ፡ በተቻለ መጠን ሕጋዊ የሆነ ምክር በአስቸኳይ ማግኘት ይኖርብዎታል - ጠበቃዎ ምክር እንዲሰጥዎት ይጠይቁት፡ ወይም ደግሞ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚሰራ ሰው የጠበቃዎች ስም ዝርዝር ይሰጥዎት ዘንድ ይጠይቁት።**

## የጥገኝነት ጥያቄዎ እና የይግባኝ ምልክታዎ በሙሉ ተቀባይነት ካጣ በኃላ፡ ያለው የድጋፍ ሁኔታ

ያቀረቡት የጥገኝነት ጥያቄ ተቀባይነት ካጣ በኃላ፡ መኖርያ ቤት ወይም ድጋፍ ለማግኘት በጣም አስቸጋሪ ይሆናል። ነገርግን እንደሚከተለው ጥቂት መንገዶች አሉ፥

### 1. የክፍል 95 ድጋፍ - የጥገኘነት ጥያቄ በጠየቁበት ጊዜ ይሰጥዎት የነበረ ድጋፍ

- ከ18 ዓመት ዕድሜ በታች የሆኑ ልጆች የ S95 NASS* ድጋፍዎ ከማለቁ በፊት ከእርስዎ ጋር የሚኖሩ፡ ልጆች ካልዎት፡ አብዛኛው ጊዜ ልጆችዎን በሙሉ 18 ዓመት ዕድሜ እስከሚያደርጉ ድረስ ድጋፉ ይቀጥላል።
- ልጆች ከሌልዎት እና፡ የጥገኝነት ጥያቄዎ ደግሞ ተቀባይነት ካጣ ከ NASS S95* ያገኙ የነበሩት ድጋፍ ከ21 ቀናት በኃላ ይቋረጣል። ይህንን በተመለከተ ደግሞ NASS* በደብዳቤ ያሳውቆታል።

### 2. **የክፍል 4 ድጋፍ** — መሰረታዊ የሆነ መኖርያ ቤት እንዲሁም ምግብ ወይም ቫውቸር።

- የNASS S95* ድጋፍዎ ኪቋረጠ በኃላ፡ ልጆች ከወለዱ ወይም ደግሞ እንግሊዝ አገርን ለቀው ለመሄድ የማይችሉ ከሆነ፡ ወይም ደግሞ ወደ አገርዎ በፈቃደኝነት እንዲመለሱ ካመለከቱ፡ የክፍል 4 ድጋፍ የማግኘት መብት ይኖርዎታል። ዝርዝር መረጃ ለማግኘት፡ እባክዎ Refugee Action's* የሚል በራሪ ጽሑፍ የSection 4* ድጋፍ የሚለውን ይመለከቱ።

### 3. የአከባቢ ባለስልጣን ድጋፍ

- በጣም ከባድ የሆነ የአካል / የአእምሮ ችግር ካልዎት ወይም ደግሞ በእድሜ ሽማግሌ / በሽተኛ ከሆኑ Local Authority* መኖርያ ቤትና ድጋፍ ሊሰጥዎት ይችላል። መጀመርያ ግን በእርስዎ ላይ ግምገማ ያደርጋሉ - ይህ ደግሞ Community Care Assessment* ተብሎ ይጠራል፡ ጥቂት ሳምንታት ደግሞ ሊወስድ ይችላል።
- ልጆች እያላችሁ፡ ነገር ግን የ S95 ወይም የ S4 ድጋፍ ለመቀበል የማይገባችሁ ከሆነ የአከባቢ ባለስልጣኑ ለልጅዎ ይጋፍ ይሰጣል፤ ነገርግን በበተሰብዎ ውስጥ ከ18 ዓመት ዕድሜ በላይ የሆነ ሰው ካለ፡ ለዛ ሰው ድጋፍ ላይሰጡ ይችላሉ።



Refugee Action registered charity number: 283660

Client information

የእርስዎ ጉዳይ እላይ ከተዘረዘሩት ነጥቦች ውጭ ከሆነ፡ መኖርያ ቤት፣ ምግብና፣ ልብሶች ለማግኘት የሚረዳዎት የአከባቢ ድርጅቶች ሊኖሩ ይችላሉ።

**ማንኛውም ዓይነት ጥያቄ ካልዎት፡ እባክዎን በዚህ ጉዳይ ላይ የሚሰራ ሰውን ይጠይቁ።**

* እነዚህ ቃላቶች የአንዳንድ ድርጅቶች የእንግሊዘኛ ስሞች፡ ወይም ደግሞ ሌሎች መተርጎም የሌሌባቸው ቃላቶች ናቸው። ምን ማለት መሆናቸውን እንዲገልጽልዎት ከፈለጉ እባክዎን ምክር የሚሰጠውን ሰራተኛ ይጠይቁ።